# ወንጀልና ሽብር

በማቴዎስ 24፡37 ጌታ ኢየሱስ ምጽዓቱ የሚሆነው “ቀኖቹ የኖህን” ቀናት ከመሰሉ በኋላ እንደሆነ ተናግሯል። ለመሆኑ የኖኅቅ ቀናት ምን ይመስሉ ነበር? “እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ። .......ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች ምድርም ግፍን ተሞላች።” (ዘፍ.6፡5፤11)

አባት ልጆቹንና ሚስቱን በበዓል ቀን መግደል፤ልጅ ወላጆቹን በአንድ ቀን መግደል፤የህጻናት ታፍኖ መወሰድና በአሰቃቂ ሁኔታ መገደል፤የሴቶች መደፈርና ግፍ በድሃ አገሮች ብቻ ሳይሆን በሰለጠኑትም አገሮች የየዕለት ዜና ከሆነ ውሎ አድሯል። ዛሬ የምንሰማው የወንጀል አይነት በኖህ ዘመንም የነበረ አይመስልም።

ወጣቶች በሚያዩት ሲኒማና በሚሰሙት የሮክ ሙዚቃ ተነድተው ሌላውን ወጣት መግደልና እንደዘመኑም ስልጣኔ በኢንተርኔት ብዙ ወጀሎች በመፈጸም ምድርን ለመኖር አደገኛ ስፍራ አድርጓታል። ባህርይን የሚያጠኑ ምኁራን እንደሚናገሩት  አንድ ልጅ 15 አመት ከመድረሱ በፊት በቴሌቪዥን 35 ሺህ ግድያዎችንና 2 መቶ ሺህ አሰቃቂ ወንጀሎችን ተመልክቷል። ወንጀል በየሲኒማው እጅግ የተወደደ ትዕይንት ሆኗል ታዲያ በገሃድ ሲመጣ ለምን እናዝናለን? ታላላቅ ተዋንያ እጅግ የገነኑት በሲኒማ ደም ማፈስስና ጭካኔን ስለሚያሳዩ ነው።





ወንጀል በህጻናት የካርቱን ሲኒማዎች ላይ ሳይቀር ሰርጎ ከገባ ሰንብቷል። "The Teenage Ninja Mutant Turtles" ፤ "The Simpsons"፤"Beavis and Butthead" ለምሳሌነት ይጠቀሳሉ። ቀድሞ ከነበረው የDisney cartoons ዛሬ ያለው እጅግ የከፋ እንደሆነ ግልጥ ነው። ይህም በልጅነት የተዘራው ወንጀል በወጣትነት እድሜ ሞልቶ እንደሚገነፍል ይሆናል።

ይህ የቴሌቪዢን ወንጀል ዘር በቅሎ ዛሬ በአሜሪካን አገር በየ25 ሰከንድ ወንጀል ይፈጸማል። በየ9 ሰኮንዶች ቤቶች ይዘረፋሉ፤ ሴቶች በየስድስት ደቂቃ ይደፈራሉ፤ በየ25 ደቂቃው የግድያ ወንጀል ይፈጸማል።  ይህ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ምልክት ነው። በዚህ አይነት ዝብርቅርቅ አለም ውስጥ ብቸኛ መጽናኛ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ነው። ጌታም ሲመጣ ምድር እውነተኛ ሰላምንና ፍትህን ታገኛለች። ስለዚህም ማራናታ አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና ልንል ይገባል!